ቡርሃን አዲስ

# የመሲኖች ዕድር

## ሰው ያልቻለው ብቸኛ እንቆቅልሽ



# የመሲሖች ዕድር

## ሰው ያልቻለው ብቻኛ እንቆቅልሽ!

ቡርሐን አዲስ

© የመፅሃፉ ሙሉ መብት የደራሲው ነው!

በህግ የተጠበቀ ነው።

2013 ዓ.ም

የመጀመሪያ እትም ነሀሴ 2013 ዓ.ም

የሽፋን ዲዛይን- +251910839307

አርትኦት- ኤልሮኢ አለማየሁ

# ምስጋና

አርታኢው ልጅ ሆነህ ትልቅ ስራ ሰርተሃል ምስጋና ይገባሃል!!!

የአስኳላዎቹ **ንግስት /ረዱ/ እና አልጋ ወራሹ /ጄክ/** በፊደል ለቀማና እርማት ተሳትፈዋል አመስግኑልኝ!

# መቅድም

ይህ መፅሐፍ አዕምሮ እንጂ ልብ-ወለድ አይደለም!

ከስሜት ሳይሆን ከዕውቀት፤ ከኹነት ሳይሆን ከምክንያት የተቀዱ ሃሳቦች የሚገዟችሁ ብቻ ዝለቁ...

# መግቢያ

" ትናንሽ ሰዎች ስለሰዎች መካከለኛ ሰዎች ስለሁነቶች ሲያወሩ ትላልቅ ሰዎች ደግሞ ስለሀሳቦች ያስባሉ፡ያወራሉ፡ይመክራሉ "ብሏልና ሶቅራጠስ፡ እናንተን እዚህ ደጅ ማግኘት ሀገሬ ከሰውም ከሁነትም ከፍ ብለው ሃሳቦች ላይ ሊዘምቱ የፈቀዱ ልጆች እንዳሏት የሚያውጅ ብስራት ነው፡ እንኳን ደስ አለኝ! (ለጊዜው አርግጠኝነቴ በራሴ ደስታ ላይ ነውና፣ ስትዘልቁ ግን ከእኔ በላይ እንደምትደሰቱ ጥርጣሬ የለኝም። :)

በእርግጥ ስለዚች መፅሃፍ ከደራሲው ጋር መምከር ከጀመርን ሰነባበትናል... ያው የተከበረችው ጊዜ ይህቺ ናትና ዛሬ እጃችሁ ገብታለች። ይህ ጥራዝ ለእኔ እንድናስብ በሚያሳስቡ ሃሳቦች የተሞላ ምናባዊ የሀሳብ አለም ጉብኝት ነው። ደራሲው በሶስት ታላላቅ ምድረ ግቢዎች የከፋፈለውን መካነ-ሃሳብ ከህይወቱ፡ ከንባቡና ከልምዱ ባካበተው እውቀት እያስጎበኘን ሊዘልቅ በቀዳሚው አፀድ ደጃፍ ላይ በተጠንቀቅ ይጠብቃችኋል። እኔ በአጭሩ የጉብኝት ካርታውን እንካችሁ ልበላችሁ።

በጠቅላላው ምናባዊ ጉብኝቱ በሶስት ትላልቅ ምድረ-ግቢዎች ውስጥ በሚካሄዱ በርካታ ንዑሳዊ የሀሳብ አንጓዎች የተከፋፈለ ሲሆን እስከአሁን ከተለመዱ የሀሳብ መፅሀፍት ለየት ባለ መልኩ ንዑሳዊ ሃሳቦችን በአንድ ወጥ ገመድ የተያያዙ ጥብቅ የቀዳሚ ተከታይነትና ትስስር ያላቸው ከማድረግ ይልቅ የአውድ ተናባቢነትና የግብ ፍሰትን ባላናጠበ መልኩ በአንድ ትልቅ መደርደሪያ ላይ በሳጥን በሳጥን ተደርገው እንደተቀመጡ ንብረቶች... በሙሉ መፅሀፉ ውስጥ እንደ አንድ አካል፣ ደግሞም ራሳቸውን ችለው መቆም እንደሚችሉ እንደወጥ የሃሳብ ቁንጣሪም ሆነው እንዲቀርቡ ተደርጓል። ይኸውም አንባቢው ወይም ጎብኚው በተመቸው ጊዜ፣ በሄደበት ቦታ፣ በያለችው ጥቂት ሰዐታት ሁሉ መካከል አንዷን ሀሳብ አንብቦ ለመረዳትና ለማሰላሰል እድል ከመስጠቱም በላይ በጉብኝቱ ላይ በሚነሱ ሃሶች ለሚፈጠር የማድረግ ተነሳሽነት በጊዜ፣ በዘርፍና በጠቀሜታ የተከፋፈለ አይነተኛ የአተገባበር አብርሆት እንዲያበረክት በማሰብ ነው። ሶስቱም አቃፊ አፀዶች በሰው ልጅ ላይ ያተኮሩ ናቸው።

1. **የሰው ልጅ፡-** የሰው ልጅን ከራሱ ማስተዋወቅ!

2. **ስለሰው ልጅ፡-** የሰው ልጅ በዙሪያው ካለው አለም ጋር ያለውንና የነበረውን መስተጋብር!

3. **ለሰው ልጅ፡-** ወቅቱንና ማንነቱን ያማከሉ የአካሄድ አቅጣጫ ጥቆማዎች... ለሰው ልጅ!

ሳላዘገያችሁ ወደጓጓችሁበት ጉብኝት ትኬታችሁን አስይዤ ልላካችሁ፤ **እያነበባችሁ አስቡ እያሰባችሁ አንብቡ!**

እኔ ከሶስቱ ግቢዎች ማዶ እጠብቃችኋለሁ......!

**አርታኢው**

## ማውጫ

### ክፍል አንድ - የሰው ልጅ!

መልስ የሆነ ጥያቄ ........ 18
የአካል ሰው! ........ 19
የአእምሮ /አንጎል/ ሰው! ........ 20
የህሊና (መንፈስ) ሰው! ........ 20
ጥቅም ........ 23
ከቅኔያት እስከ ኪነ-ህንጻ ያለው የጥበብ ክሂሎት ፋይዳው ምንድን ነው? ........ 25
ጥቅም ለአካላችን ወይስ ለመንፈስ? ........ 27
ዉበት… የመንፈሳዊነት አንዱ አንጓ ........ 27
ሰውና ኢትዮጵያዊ ሰው ........ 28
ለአንድ ኢትዮጵያዊ! ........ 28
ኢትዮጵያዊነት ባይሰማው ምን ይጎዳል? ........ 28
በምክኒያት ወይም በባህል የምንለብሰው የሰው መሆን ጸጋ ........ 31
ለአስተውሎት እንዲያግዘን ........ 35
እንደ ኢትዮጵያዊ ........ 38
ባህላዊና ዘመናዊ መንገዶች ........ 39
እንደማስታወሻ! ........ 40
ስሜትና ዕውቀት ........ 42
ሁለት ግለሰቦች ድብድብ የሚያደርስ ጥል የሚያነሱት በእውቀት ወይስ በስሜት? ........ 42
እንደመሻገሪያ ........ 44
ሰው በተፈጥሮው የሚያደላው ለነጠላ እሱነቱ ወይስ ለቡድን ማንነቱ? ........ 45

ስሜት ወለድ ሰውና ምክኒያት ወለድ ሰው ........ 45
እስኪ የትኛውን ለማመን ይቀላል? ........ 49
እጥር ምጥን ስናደርገው ........ 50
**ክፍል ሁለት - ስለሰው ልጅ!**
ጭምጭምታ እንደማስታወቂያ ሳይንስ ........ 56
ህይወት ከሳይንስ በላይ ናት! ........ 59
ኃይማኖት ........ 60
ሮሜ 5፡19 ........ 60
ቁርአን 5፡32 ........ 60
ራልፍ ዋልዶ ኤመርሰን ........ 60
ሶቅራጠስ ........ 61
ኃይማኖት አንዱ ኢ-ምክኒያታዊ ግን አሳማኝ የሰው ልጅ እሴት ነው። ........ 62
ከኃይማኖት የምንማረው ........ 68
የታላላቆቹ ስፒኖዛና ማርክስ ያልተጠበቁ ድክመቶች ምን ነበሩ? ........ 70
የስፒኖዛ ዘመን በኢትዮጵያ የነበረው ድባብ! ........ 70
ስፒኖዛ (1632-1677) ........ 71
ካርል ማርክስ ........ 72
የሊቃውንቱ ተመሳሳይ ድክመት ........ 72
ስፒኖዛ የነበረው ግምት ........ 72
ከነዚህ ግዙፍ ፈላስፎች ደካማ ጎኖች ተነስተን እኛን እንመትር እንግዲህ... ........ 74
ከስጋ ስሜታዊነት እስከ ልቦናዊ ስሜት ........ 75
ኢ-ምክኒያታዊነት ........ 77
ከምክኒያት አድማስ ባሻገር ያለ እንግዳ ማንነት! ........ 77
እዚህ ኦሪጂናል ስሜቴ ውስጥ ቆሜ ምን ላስብ እችላለሁ? ........ 78

ታሪክ እንዴት ካሁን ይጀመራል? ... 81

የስርዓትና የግለሰቦች መምታታት አለ! ... 81

21ኛው ክፍለ ዘመንና የሉኣላዊ ሀገራት መፍረስ አይቀሬነት ስጋት ... 84

የሽብርተኝነት ዘመቻ (war on terror) ስውር አጀንዳዎች ለናሙና! ... 85

ቀጠናዊነት (regionalism) ... 85

ግሎባላይዜሽን እና ግሎባሊዝም ... 87

በአለም ላይ እንዲሆን የሚጠበቀው የአዲሱ ዓለም መልክ ... 90

መጠን ... 92

እርግጠኛ የሚያደርገን ምንድን ነው? ... 94

ሰውን ከባህሉ ነጻ ማውጣት እንደስልጣኔ ወይስ እንደቀውስ? ... 101

የሩጫ ወድድርን ለማስጀመር... ... 103

እውቀት ... 104

እውቀት ግን ምንድን ነው? ... 105

1. መንጋ ማህበረሰብ (crowd society) ... 106
2. የግለሰብ አማልክት (hero worship) ... 107
3. መንጋ ባህል (popular culture) ... 107
4. ቡድንተኛ ጽንፍ (thought polarization) ... 108
5. ሸቀጤ-ማህበረሰብ (consumer society) ... 108
6. የህገ-ልቦና መሞት (death of moral culture) ... 108
7. ሰውን እንደጥሬ እቃ የሚያመርት የትምህርት ፍልስፍና ... 109

ከሚያግባባን ለመነሳት... ... 110

1. ራስን ማብቃት የማያስችል ስርዓት መፍጠር ... 110
2. የተፈጥሮ ሀብት አላቂ ነው በሚል ፕሮፖጋንዳ ፍርሃት ማንገስ ... 111
3. የጥበብን ዋጋ ማሳነስ፤ ደራሲያን፣ ሰዓሊያንና የሞራል ፍልስፍናን መተው 112

4. ኃይማኖት የሰውን ልጅ ከስልጣኔ እንዳስቀረ አስመስሎ ማቅረብ.......... 113
የሰዓት ፊርማ ጉዳይ.......... 113
መንጋ ወይስ አጀብ.......... 115
"መንጋ" የዘመናዊ ገበያ ቃል.......... 116
ትምህርት ቤት.......... 118
ዊንስተን ቸርችል /የቀድሞው የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስቴር/.......... 118
ሰውን ከማህበረሰብ ወደ ግለሰብ የሚያመርት ኢንዱስትሪ.......... 118
ኔል ፖስት ማን.......... 118
ኑአም ቾምስኪ.......... 120
ትምህርት፣ እውቀት፣ አስተውሎት.......... 126
ትምህርት፤ የህዝብ ትምህርት ቤት፣ ታሪክና ዓላማ.......... 129
ልጆች ለምን ትምህርት ይጠላሉ?.......... 132
ዘመናዊ ትምህርት፣ አነሳስና ወቅታዊ እውነታ.......... 135
አዉሮፓ.......... 135
የሉተር ሌጋሲ ምን ነበር?.......... 138
አስትሪያ ካልቪን.......... 139
ሀገራት ይህን የፕሩሻን የትምህርት ሞዴል ለምን ተቀበሉት?.......... 141
የህግ የበላይነት ወይስ የገዢዎች የበላይነት?!.......... 143
የአሮጌና አዲስ ዓለም ፈሊጥ.......... 143
ሀምሌ አመሻሽ 1914.......... 143
ሁለት አይነት የዓለም ስርዓት እሳቤቶች ነበሩ!.......... 145
ህግና ገዢዎች.......... 147
ያለፕሮፓጋንዳ የሰረጸ ዘመናዊ ዲሞክራሲ የለም!.......... 151
የህዝብ ወቅታዊ ስሜትና አመራር ሳይንስ (public opinion and perception management).......... 152

የሳይኮሎጂና ፖለቲካ ጋብቻ! ........ 153

ዶክተር ኢዊን ካሜሩን ........ 154

የሳይኮሎጂና ቢዝነስ ጋብቻ ........ 156

የሳይኮሎጂና ትምህርት ጋብቻ ........ 156

ባህልን የተቃረነ ባህል ፈጥሮ ለማስረጽ የሳይኮሎጂ ሚና ........ 157

ሶሻል ዳርዊኒዝም ........ 159

ዩጀኒክስ ........ 161

ለትዝብት እንዲረዳን! ........ 163

ጥያቄ እጠብቃለሁ፡ ........ 164

ቢሄቪየሪዝም ........ 166

ፍሬያችን! ........ 167

ሳይንሳዊ አመራር! (scientific management) ........ 168

የቢሄቪየሪዝም አስተሳሰብ በሳይንሳዊ አመራር ውስጥ! ........ 168

ሞለኪውላር ባዮሎጂና ጀነቲክስ! ........ 169

እውን ድህነት የጀነቲክስ ዉጤት ነው? ........ 169

"አፍሪካዊን" ........ 169

ማጠቃለያ!! ........ 174

**ክፍል ሦስት - ለሰው ልጅ!**

እንዲህ እንድንሆን ተጠያቂው ማነው? ........ 176

ለምን? ........ 176

ለትዝብት ያህል…! ........ 178

መላ መዘየድ የግድ ይሆናል! ........ 180

ታሪክ ካፈራቸው በጎ ጠቢባንና እኩይ ጠቢባን የትኞቹ ይበዛሉ? ........ 181

የትውልድ ሸክም ማን ላይ ይጫን? ........ 185

ሀገራት ይፈርሳሉ… ይገነባሉ… ህዝብ ግን አይተካም!! ........................................ 185
ትራጂዲ 1፡ ዩጎዝላቪያ /ቦዝኒያ, ኮሶቮ፡ ክሮሺያ…/ ........................................ 187
ትራጂዲ 2፡ ሩዋንዳ፡ አንድ የነበረን ህዝብ መከፋፈል እንዴት ቀላል እንደሆነ ........................................ 191
ፌስቡክ የወለዳቸውን ጅኖሳይዶች ደግሞ ለማሰብ እንሞክር ........................................ 193
ዲሞክራሲና ፌስ-ቡክ ........................................ 193
ተከፋይ አክቲቪስትና ተከፋይ ኢሊት ........................................ 195
ኢትዮጵያ ከዩጎዝላቮች የተሻለ እድል ምን አላት? ........................................ 198
1. ከኃይማኖት መልካችን እንጀር ........................................ 199
2. ከጎሳ መልካችን እንጀር ........................................ 203
3. ከርዕዮት ዓለም አይታችን እንጀር ........................................ 205
4. ከስራችን ኃላፊነት እንጀር ........................................ 207
የሀገር ፍቅር ........................................ 209
እነዚህንና መሰል እንከኖቻችንን ካስቀረን ኢትዮጵያ የታላቅነትና አንድነት እድሏ ሰፊ ነው! ........................................ 209
እዚህ ላይ የምናስተውለው ምንድን ነው? ........................................ 211
መሲሕ፣ መሲሓዊነት እና መሲሓውያን ........................................ 213

# ክፍል አንድ

## የሰው ልጅ

## ደራሲው ቡርሃን አዲስ

ትውልድና ዕድገቱ ደሴ፤ ትምሕርቱን ባሕር ዳር ኑሮውን ሸገር ላይ ያደረገ ፈላስፋ፣ ደራሲ፣ የፊልም ጸሐፊና አዘጋጅ ነው። በቅርቡ ታትሞ ለንባብ የበቃው "የዘር ካርድ" የተሰኘውን መጽሐፍ ጨምሮ ከሠላሳ በላይ መጽሐፍት ለተደራሲያኑ ያደረሰ፦ "ዓለም በቃኝ" እና "ውኃና ወርቅ" የተሰኙ የፊልም ሥራዎቹም ለዕይታ የበቁለት፦ በፍልስፍናዊ የመድረክ ዲስኩሮቹም ይታወቃል።



"በየራሳችን ላይ አብዮት እንጀምር ከዛ | ሰላማዊና ጥበብ ፈንጣቂ የልዕልና ዕድር እንመሠርታለን።"

ጉዳያችን የየራስ፣ የየቡድንና የየጎራችን ጉዳዮች እንዲከበሩ ከማድረግ ተሻግሮ የሌሎች አቻ ወገኖችንም ክብር እንዲከበር አድራጊ ታላቅነት እንድናስብ ነው። የታላቅ ሀገረ-ቤታችን መሪ የሚሆን የኔ ብቻ ሳይሆን የሁላችንም ጉዳይ የሚያሳስበው ከፍ ያለውን ልዕልና አሻግሮ የሚያይ የጥበብ ሙሊት ያነጸውን ነጻ አዉጪ ነው እንድናስብ የከጀልነው።

"የመሲኖች ዕድር" በማለት የከፈትነውን በቁጥር ጥቂትም ይሁን ብዙ ለሌሎች ነጻነትና እኩልነት ታጋይ ሆነን የተሰየምን ሁሉ ሰብሰብ ብለን ስለመምከርና የሁላችን የሚሆን ታላቅ የአርነት መንገድ ጥርጊያ ስለመሥራት መምከር እንድናስተውል ነው ሁላችንም በመጀመሪያ ራሳችንን ነጻ ማውጣት ወይም በራሳችን ላይ መሲኅ መሆን አለብን።

ኃይማኖታዊ፣ ጎሳዊ ወይም መሰል የፍላጎት ጥያቄ እንደጎጠኝነት የሚታይ ርዕስ አይደለም። ሁሉም ለባህሉ ወይም ላደገበት ማንነቱ የሚማረክበት እውነታ አለውና።

የሽፋን ገጽ ቀንበር MULER 0913450005

ዋጋ 180.00 ብር
$ 30

ኪስታ ማተሚያ ቤት
0911687770